የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

# የስታርታፕ እና የስታርታፕ ምህዳር ገንቢ ስያሜ አሰጣጥ መመሪያ
## ቁጥር 1154/2019

ጥቅምት/2019 ዓ.ም

# <u>መመሪያ ቁጥር 1154/2019</u>

## <u>የስታርታፕ እና የስታርታፕ ምህዳር ገንቢ ስያሜ አሰጣጥ መመሪያ</u>

ስታርታፕ እና የስታርታፕ ምህዳር ገንቢዎች አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎችን እንዲያገኙ ለማድረግ የሚያስችል ወጥነት ያለው ስርዓት በመዘርጋት ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤ የፈጠራ ሃሳብ ባለቤቶች አስፈላጊ የሆኑ ማትጊያዎችንና ጥቅሞችን እንዲያገኙ ያላቸውን ሃሳብ በማቅረብ ግልጽ በሆነ መመዘኛ መሠረት ገለልተኛና በዘርፉ ክህሎት ባላቸው ባለሙያዎች እንዲመዘኑ በማድረግ የስታርታፕ ስያሜ እንዲያገኙ ግልጽ የሆነ የአሰራር ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ሃሳባቸውን በፈጠራ በማዳበር ጥረት ለሚያደርጉ ሰዎች ያለባቸውን የገንዘብ እጥረት በመቅረፍ የፈጠራ ስራዎቻቸውን ማበልጸግ እንዲችሉ ለማገዝ የሚረዳ ድጋፍ ማድረግ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ በማስፈልጉ፤

ከስታርታፕ እና ስታርታፕ ምህዳር ገንቢ ስያሜ አሰጣጥና አተገባበር ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ቅሬታዎች ግልጽ፣ ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋ እና ተገማች የሆነ የቅሬታ አቀራረብ እና አፈታት ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በስታርታፕ አዋጅ ቁጥር 1396/2017 አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

### 1. <u>አጭር ርእስ</u>

ይህ መመሪያ “**የስታርታፕ እና የስታርታፕ ምህዳር ገንቢ ስያሜ አሰጣጥ** መመሪያ ቁጥር 1154/2019” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. <u>ትርጉም</u>

የቃሉ ወይም የሀረጉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"አዋጅ"** ማለት የኢትዮጵያ ስታርታፕ አዋጅ ቁጥር 1396/2017 ነው፡፡

2) **"የጋራ የስራ ቦታ"** ማለት ለስታርታፖች በአባልነት ወይም በክፍያ የሚሰጥ መሰረታዊ የቢሮ አገልግሎትን፣ የስራ መሳሪያዎችንና የትስስር አገልግሎቶችን አቀናጅቶ የሚያቀርብ የንግድ ድርጅት ወይም ተቋም ነው፡፡

3) **"ኮሚቴ"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የተቋቋመው የብሄራዊ የስያሜ ኮሚቴ ነው፡፡

4) **"ስያሜ እድሳት"** ማለት ስታርታፑ ወይም የስታርታፕ ምህዳር ገንቢው የተሰጠው ስያሜ ጊዜውን ሲጨርስ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ወቅቱን ጠብቆ በደረጃው መሰረት የሚደረግ የስያሜ እድሳት ነው፡፡

5) **"የብቃት መስፈርት" ማለት ለ**ስታርታፕ ወይም የስታርታፕ ምህዳር ገንቢው እንደ ስያሜ ለማግኘት፣ ለመቀጠል ወይም እድሳት ለማግኘት የሚጠየቁ መደበኛ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ናቸው፡፡

6) **"የስያሜ ደረጃ"** ማለት በስታርታፕ ኢኮሲስተም ውስጥ ስታርታፑ ያለውን እድገት እና ደረጃ የሚያመላክት ስያሜ ነው፡፡

7) **"መጀመሪያ ደረጃ ስታርታፕ"** ማለት የፈጠራ ሃሳቡን በማረጋገጥ እና የዕድገት መሰረትን እየገነባ ያለ አዲስ የተመሰረተ ስታርታፕ ነው፡፡

8) **"ድህረ መጀመሪያ ደረጃ ስታርታፕ"** ማለት ምርቱን ወይም አገልግሎቱን በገበያው ውስጥ ሞክሮ ከገበያው ጋር መጣጣሙን በተሳካ ሁኔታ ያረጋገጠ እና ወደ እድገት እየተሸጋገረ ያለ ስታርታፕ ነው፡፡

9) **"ተመንዳጊነት እና ሽግግር ደረጃ ስታርታፕ"** ማለት የምርት ለገበያ ተስማሚነት፣ ፈጣንና ተገማች እድገት ያለው ገበያውን ማስፋፋት፣ የትግበራ ፍጥነትን ማጎልበት እና ገቢን ማሳደግ ላይ ያተኮረ እንዲሁም ከስታርታፕ አድጎ ለመውጣት ዝግጅት ላይ ያለ ስታርታፕ ነው፡፡

10) **"ፕሮፖዛል"** ማለት ስታርታፑ የእድገት ደረጃውን ማዕከል በማድረግ የፈጠራውን የንግድ ስራ ሃሳብ እንዴት እንደሚሰራ የሚፈታውን ችግርና መፍትሄ የቢዝነስ ሞዴል እና የገበያ ትንተና የሚገልጽ እንዲሁም እንዴት እንደሚያድግ በዝርዝር የሚገልጽ የጽሁፍ እቅድ ነው፡፡

11) **"ሽግግር"** ማለት ስታርታፖች ከአንዱ የእድገት ደረጃ ወደ ቀጣዩ የእድገት ደረጃ የሚያደርጉት ለውጥ ነው፡፡

12)**“የምርት ወይም የአገልግሎት ናሙና (ፕሮቶታይፕ)”** ማለት በዝቅተኛ ጥረት፣ ጊዜ እና ወጪ ለተጠቃሚዎች አገልግሎት መስጠት የሚችል እና ከገበያ ለመማር የሚያስችል የምርት ናሙና ነው፡፡

13)**“ቅድመ ግምገማ”** ማለት አመልካቹ ለሚያመለክትበት ጉዳይ ከስያሜ ኮሚቴ ግምገማ በፊት አስፈላጊውን ሰነድ ስለሚሟላቱ የሚታይበት ሂደት ነው፡፡

14)**“ሚኒስትር** ወይም **ሚኒስቴር”** ማለት እንደየቅደም ተከተላቸው የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር እና ሚኒስቴር መስሪያቤቱ ማለት ነው፡፡

15)በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

16) ሰው ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

17) በአዋጁ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላትና ሀረጋት ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ስታርታፕ አዋጅ መሰረት ስያሜ ለማግኘት በሚፈልጉ ስታርታፕ ወይም የስታርታፕ ምህዳር ገንቢዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. <u>መርህ</u>

ይህ መመሪያ በሚከተሉት መርሆች ላይ ተመስርቶ የሚተገበር ይሆናል፡-

1) ስያሜ አሰጣጡ የስታርታፕ ምህዳር ኢንደስትሪ ሙያውን ስታንዳርድ የጠበቀ መሆን፤
2) ብቃትን መሰረት ያደረገ ስያሜ አሰጣጥ፤
3) የስያሜ አሰጣጥ በማመልከቻ ቅደም ተከተል መሰረት መስተናገድ፤
4) ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት ቀልጣፋ ውሳኔ አሰጣጥ፤

5. <u>ሚስጥራዊነት</u>

በአመልካች እና ስያሜ በተሰጣቸው ስታርታፕና ምህዳር ገንቢ የሚቀርቡት ሁሉም መረጃዎች በሚኒስቴሩ፣ በብሄራዊ የስያሜ ኮሚቴ እና በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሚስጢራዊነታቸው በግል ዳታ ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 1321/2016 መሰረት መጠበቅ አለባቸው፡፡

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>ስያሜ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ</u>

6. <u>የማመልከቻ ፕላትፎርም</u>

ሚኒስቴሩ፦

1) ስያሜ ለማግኘት ለሚያመለክት ስታርታፕ ወይም ስታርታፕ ስነምህዳር ገንቢ ስያሜ ለመስጠት የሚያገለግል ፕላትፎርም ይዘረጋል፡፡
2) ፕላትፎርሙ ስራ መጀመሩን ተደራሽ በሆነ ማህበራዊ ሚድያ በኩል ማሳወቅ አለበት፡፡
3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴሩ ለዚሁ አላማ በተዘጋጀ ፕላትፎርም ላይ ዝርዝር የማመልከቻ መስፈርቶችን ያስቀምጣል፡፡

7. <u>የማመልከቻ ሂደት</u>

1) በአዋጁ አንቀጽ 9 እና አንቀጽ 17 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ስያሜ ለማግኘት የሚፈልግ ስታርታፕ ወይም ስታርታፕ ስነምህዳር ገንቢ ማመልከቻውን በሚኒስቴሩ በተዘጋጀ ፕላትፎርም ላይ ኦንላይን ማመልከት አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው ማመልከቻ በቀረበ አምስት የስራ ቀናት ውስጥ ቅድመ ግምገማ በማድረግ ለስያሜ ኮሚቴ ይቀርባል፡፡
3) የሚቀርበው ማመልከቻ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 22 እና 28 ላይ የተገለጹ መስፈርቶችንና ተያያዥ ሰነዶችን በማሟላት መቅረብ ይኖርበታል፡፡
4) አመልካቹ የሲስተም ችግር ባጋጠመው ጊዜ በተቻለ ፍጥነት ለሚኒስቴር መስሪያቤቱ ማሳወቅ አለበት፡፡
5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካቹ የሲስተም ችግር ሲያጋጥመው ለሚኒስቴር መስሪያቤቱ በአጭር የስልክ መልእክ፣ በስልክ ጥሪ፣ በኢሜል ወይም በመሳሰሉት መንገዶች ማሳወቅ ይችላል፡፡
6) በአዋጁ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ስታርታፑ ለማመልከት ከዚህ በታች የተዘረዘሩ መረጃዎችን ማሟላት አለበት፡፡
   ሀ) ኢኖቬሽንን ተግባራዊ የሚያደርግ፣ የቴክኖሎጂ ወይም በቴክኖሎጂ የታገዘ፣ ተመንዳጊ እና የገበያ መዋቅር የሚለውጥ ስለመሆኑ ማብራሪያ፤
   ለ) የአባላት ብዛት፣ የመስራች እና አባላት ፋይዳ መለያ ቁጥር፤
   ሐ) ደረጃውን ማዕከል ያደረገ የስታርታፕ ሀሳብ ፕሮፖዛል፤

መ) አጭር የተጠቃለለ ፕረዘንቴሽን፤

ሠ) ስታርታፑን ምርት፣ አገልግሎት ልዩ የሚያደርገውን ማስረጃ ዝርዝር፤

ረ) በሃሳቡ ዙሪያ የስታርታፕ መስራቹን ታሪካዊ ዳራ የሚገልጽ እና ያሰባሰበው ፈንድ ወይም ሌሎች ድጋፎች፤

ሰ) የሚገኝበት ደረጃ የሚያሳይ ማስረጃ፤

ሸ) ቃለመሀላ መሙላት፤

ቀ) የውጭ ስታርታፕ ከሆነ ከፋይዳ በስተቀር ከላይ የተገለጹትን መስፈርቶች እና ፓስፖርት፣ የመጣበት ሀገር እና ስታርታፑ የሚሰራበት ከተማ፤

7) በአዋጁ አንቀጽ 17 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የስታርታፕ ምህዳር ገንቢው የሚያቀርበው ማመልከቻ

ሀ) የባለቤት (የድርጅቱ) ስም፤

ለ) በሚያስተናግዱት የስታርታፕ ደረጃ ላይ ያላቸው የስታርታፕ ፕሮግራም፤

ሐ) በአዋጁ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ (ሐ) መሰረት የብቃትና የጥራት ደረጃ መመዘኛ ማሟላቱን የሚያመላክት ማስረጃ የያዘ መሆን አለበት፡፡

## 8. የማመልከቻ ምላሽ አሰጣጥ

1) ሚኒስቴሩ ከአመልካች ለሚቀርብ የስያሜ ማመልከቻ በ30 የስራ ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀኑ የሚቆጠረው ቅድመ ግምገማ ከጨረሰበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡

## 9. የፕላትፎርም አጠቃቀም

1) አመልካች ማመልከቻውን በፕላትፎርሙ ሞልቶ ሲጨርስ በትክክል ስለመሙላቱ እና ለቅድመ ግምገማ እንደቀረበ የሚገልጽ ማረጋገጫ በፕላትፎርሙ ላይ ይገለጻል፡፡

2) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ቅድመ ግምገማውን ሲጨርስ ቀጣዩን ሂደት በፕላትፎርሙ መከታተል ይችላል፡፡

3) ሚኒስቴሩ የፕላትፎርሙን ዝርዝር አጠቃቀም በተመለከተ የውስጥ የአሰራር ማኑዋል ያወጣል፡፡

**10.<u>የምስክር ወረቀት</u>**

1) ሚኒስቴሩ በአዋጁ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ተቀባይነት ያገኘ ማመልከቻ መረጃውን በመያዝ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡
2) በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለስታርታፕ የሚሰጠው የምስክር ወረቀት፡-

   ሀ) የንግድ ፈቃድ ወይም የንግድ ምዝገባ ካለው

   ለ) የአገልግሎት ጊዜ

   ሐ) በህጋዊ ማህተም የተረጋገጠ መሆን

   መ) ልዩ የሰርተፊኬት ቁጥር

   የያዘ መሆን አለበት፡፡
3) ለስታርታፕ ምህዳር ገንቢው የሚሰጠው የምስክር ወረቀት በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ላይ የተጠቀሱትን መያዝ ይኖርበታል፡፡
4) ለስታርታፕ ወይም ለስታርታፕ ምህዳ ገንቢው የሚሰጠው የምስክር ወረቀት ዲጂታል ሰርተፊኬት መሆን አለበት፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ብሄራዊ የስያሜ ኮሚቴ አወቃቀርና አገልግሎት</u>

**11.<u>የብሄራዊ ስያሜ ኮሚቴ አባላት</u>**

1) በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከተቋማት የሚላኩ አባላት በተቋሙ በሃላፊነት ደረጃ ላይ ያሉ እና በሚወከልበት ዘርፍ እውቀት ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
2) ሚኒስቴሩ በአዋጁ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1(በ) መሰረት የኮሚቴ አባል ለምክርቤቱ አቅርቦ በማስወሰን ለተሰየሙት የኮሚቴ አባላት በደብዳቤ ያሳውቃል፡፡

**12.<u>የአገልግሎት ዘመን</u>**

የኮሚቴው የአገልግሎት ዘመን 2 አመት ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ ለአንድ ዙር ሊራዘም ይችላል፡፡

## 13.ስብሰባ እና የውሳኔ አሰጣጥ

1) ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑ በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ ይቆጠራል፡፡
2) ሁሉም የኮሚቴው አባላት እኩል ድምጽ የመስጠት መብት አላቸው፡፡
3) የኮሚቴው ውሳኔ በስምምነት ወይም በድምጽ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጹ እኩል በኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

## 14.የጥቅም ግጭት

1) ማንኛውም የኮሚቴ አባል ስራ ከመጀመሩ በፊት በተሰጠው ሥራ ላይ ገለልተኛነቱን ሊጎዳ ወይም እንደሚጎዳ ሊታይ የሚችል ማንኛውንም የግል፣ የፋይናንስ፣ የሙያ ወይም የንግድ ጥቅም ወይም ግጭት ካለ ማሳወቅ እንዳለበት የሚያስገድድ ቅጽ በመሙላት በፊርማው ማረጋገጥ አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ አባሉ የሚያሳውቀው የጥቅም ግጭት እንዳለ እንዳወቀ ከሚመለከተው ግምገማ ወይም ውሳኔ በፊት ማሳወቅ አለበት፡፡
3) የጥቅም ግጭት እንዳለው ያስታወቀ የኮሚቴ አባል ከተመለከተው ግምገማ ወይም ውሳኔ ላይ ተሳትፎ እንዳያደርግ መደረግ አለበት፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተገለጸው ቅጽ የመመሪያው አባሪ ቁጥር 1 ሆኖ ተካቷል፡፡

## 15.ከአባልነት ስለመነሳት

ማንኛውም የኮሚቴው አባል በሚከተሉት ምክንያቶች ከአባልነት ይነሳል፤እንዳግባብነቱ በሌላ አባል ይተካል፡፡

1) በጤና እክል ምክንያት ስራውን ሊሰራ የማይችል ከሆነ ወይም በሞት ከተለየ፤
2) የስነምግባር ጉድለት ከታየበት እና ለማረም ጥረት የማያደርግ ከሆነ፤
3) ከተወከለበት ተቋም የለቀቀ ወይም የተሰናበተ ከሆነ፤

## ክፍል አራት

## የስታርታፕ ተዋንያን ተግባርና ሃላፊነት

### 16.የሚኒስቴሩ ተግባርና ሃላፊነት

በአዋጁ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡

1) ለኮሚቴው አባላት የሙያ አበል ክፍያ ይፈጽማል፡፡
2) የመስሪያ ቦታ፣ የስራ መሳሪያ እና ሌሎች ለስራው አስፈላጊ የሆነ ቁሳቁስ እንዲሟላ ይደረጋል፡፡

### 17.የኮሚቴው ተግባርና ሃላፊነት

ኮሚቴው በአዋጁ የተሰጠው ተግባርና ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1) በፕላትፎርሙ የቀረቡ ማመልከቻዎችን ይመረምራል፡፡
2) በተቀመጠው መመዘኛ መሰረት ስያሜ ለማግኘት ብቁ የሆኑትን እና ያልሆኑትን አመልካቾች ውጤትና ዝርዝር መረጃ ለሚኒስቴሩ ይልካል፡፡
3) በዘርፉ እውቀት ያላቸውን ባለሙያዎች እንዲሳተፉ ሊያደርግ ይችላል፡፡
4) ለግምገማ የሚጠቀምባቸውን ግልጽና ወጥ የሆኑ መመዘኛዎች የያዘ የውስጥ አሰራር በማዘጋጀት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

### 18.የስታርታፕ ተግባርና ሃላፊነት

በአዋጁ አንቀጽ 12 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1) በመጀመሪያ የእድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ ስታርታፕ እድሳቱን ለማግኘት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ ከተቀመጡት መስፈርቶች ውስጥ ከ70% በላይ ውጤት ማግኘት አለበት፡፡
2) በድህረ መጀመሪያ የእድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ ስታርታፕ ወደ ቀጣይ የእድገት ደረጃ ለመሸጋገር በዚህ መመሪያ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (2) ላይ ከተቀመጡት መስፈርቶች ውስጥ ከ80% በላይ ውጤት ማግኘት አለበት፡፡
3) በተመንዳጊ እና ሽግግር የእድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ ስታርታፕ የድጋፍ ቀጣይነት ለማግኘት ከሽግግር ቀደም ብሎ ባለው የአንድ አመት አፈጻጸም ላይ ሆኖ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 21

ንዑስ አንቀጽ (3) ላይ ከተቀመጡት መስፈርቶች ውስጥ ከ85% በላይ ውጤት ማግኘት አለበት፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) ከተገለጸው በታች አፈጻጸም ሲያጋጥም በበቂ ምክንያት የተደገፈ የድጋፍ ጥያቄ ለሚኒስቴሩ በማቅረብ ወሳኔ ሊያገኝ ይችላል፡፡
5) ስያሜ ያገኘ ስታርታፕ ባገኘው ደረጃ መሰረት በየስድስት (6) ወሩ የአፈጻጸም ሪፖርት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

## 19.የስታርታፕ ምህዳር ገንቢው ተግባርና ሃላፊነት

በአዋጁ አንቀጽ 18 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1) ስያሜ ላገኘበት የብቃት ዳሰሳ መስፈርት ምዘና 85% በላይ አሟልቶ መገኘት አለበት፡፡
2) አድሎአዊ አለመሆኑን፣ የሚደረጉ ድጋፎች ግልጽ በሆነ ስታንዳርድ መፈጸማቸውን በተዘጋጀ የቃለመሀላ ቅጽ ማረጋገጥ አለበት፡፡
3) ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው የፕላትፎርም አጠቃቀም ማኑዋል መሰረት መጠቀም አለበት፡፡
4) የስራ ውጤታማነት በጊዜ፣ በጥቅም ላይ በዋለ ሃብት ወይም ወጪ፣ በተገኘ ውጤት የተመሰረተ ግምገማ እና ክትትል ማድረግ፤ እና
5) ስለአፈጻጸሙ አመታዊ ሪፖርት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

# ክፍል አምስት

# የስታርታፕ ስያሜ የእድገት ደረጃ፣ የብቃት መስፈርትና እድሳት

## 20.የስታርታፕ ስያሜ ደረጃ

1) በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት ለስታርታፕ የሚሰጠው ስያሜ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ደረጃዎች ይኖሩታል፡፡

   ሀ) የመጀመሪያ ደረጃ ስታርታፕ

   ለ) ድህረ መጀመሪያ ደረጃ ስታርታፕ

   ሐ) ተመንዳጊነት እና ሽግግር ደረጃ ስታርታፕ

2) በአዋጁ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመጀመሪያ ደረጃ ስታርታፕ ሁለት ዓመት፣ ድህረ መጀመሪያ ደረጃ ስታርታፕ አራት ዓመት እና የተመንዳጊነት እና የሽግግር ደረጃ ሁለት ዓመት የእድገት ደረጃ ጊዜ ይኖራቸዋል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ስታርታፑ ከአንዱ የእድገት ደረጃ ወደ ሌላኛው የእድገት ደረጃ ለመሸጋገር ያለውን የአፈጻጸም ሪፖርት እና ማመልከቻ አያይዞ ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡

## 21.<u>የስታርታፕ ብቁነት መስፈርት</u>

በአዋጁ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት ማንኛውም ስታርታፕ ለዕድገት ደረጃው ብቁ ለመሆን ከዚህ በታች የተዘረዘሩ መስፈርቶችን ማሟላት ይጠበቅበታል:-

1) **የመጀመሪያ ደረጃ ስታርታፕ**

በዚህ ደረጃ የሚገኝ ስታርታፕ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡፡

ሀ) በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የስታርታፕ ጽንሰ ሃሳብ ያለው፣ ነባራዊ የሆነ ችግርን ወይም ክፍተቱን የተገነዘበ እና ችግሩን ወይም ክፍተቱን የለየ ከሆነ 30% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ለ) በዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ላይ የተጠቀሰውን ችግር ወይም ክፍተት ለመፍታት የሚያስችል መፍትሄ ያዘጋጀ ከሆነ 10% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ሐ) የተደራጀ መስራች መኖሩን የሚያሳይ ሰነድ ማቅረብ ከቻለ 10% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

መ) በገበያ ውስጥ ለመሞከር የሚያስችል መሰረታዊ የምርት ወይም የአገልግሎት ናሙና ማቅረብ የቻለ 15% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ሠ) መሰረታዊ ምርት ወይም አገልግሎት ወደ ገበያ የመግባት ስልትን መቀየስ፣ ለገበያ ፍላጎት ተስማሚ ምርት (pmf) የመጀመሪያ ዙር ተግባራዊ ፍተሻ ማስረጃ ማቅረብ ከቻለ 10% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ረ) በገበያው ግብረ-መልስ መሰረት ገቢን ለማመንጨት አዲስ መንገድ ሲያስፈልግ የስልት ለውጥ ማድረግን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ከቻለ 10% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ሰ) ስታርታፕ መስራቹ መሰረታዊ የምርት ወይም የአገልግሎት ሀሳቡን ወደ ተግባር ለመቀየር፣ የገበያ ጥናት ለማከናወን ከራሱ ወይም ከቤተሰቡ ወይም ከጓደኞቹ ወይም ከኢንቨስተር ወይም ከግራንት ሰጪ አካላት ፈንድ ያገኘ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ ከቻለ 15% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

2) **ድህረ መጀመሪያ ደረጃ ስታርታፕ**

በዚህ ደረጃ የሚገኝ ስታርታፕ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡፡

ሀ) በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (1) እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ረ) መሰረት መሰረታዊ ምርት ወይም አገልግሎትን ለገበያ ፍላጎት ተስማሚ ምርትን (pmf) በመጠቀም ቀጣይነት ያለው የተጠቃሚ ፍላጎትን መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ከቻለ 25% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ለ) በገበያው ውስጥ ያሉ ተጠቃሚዎችን መለየት እና በበቂ ሁኔታ የተደራጀ የቢዝነስ ሞዴል መኖር እና ወደ ገበያ የመግቢያ ስልትን ተግባራዊ ማድረ የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረቡ ከተረጋገጠ 15% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ሐ) ስታርታፑ ምርትን ወይም አገልግሎቱን ለተጠቃሚዎች በማቅረብ ገቢ ማግኘት መጀመሩን እና ኢኮኖሚያዊ እሴት መፍጠሩን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ከቻለ 20% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

መ) ስታርታፑ ምርቱን ወይም አገልግሎት ወደ ገበያ ለማስገባት እና ለማደግ ከኢንቨስተሮች እና ከሌሎች ፈንድ አድራጊዎች ፋይናንስ ማግኘቱን ወይም ድጋፍ ሳያስፈልገው በውስጥ ገቢው ቀጣይነት ያለው ኢንቨስትመንት ማድረጉን እና የምርት ወይም አገልግሎት እድገት እና መስፋፋት ስለመኖሩ የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ከቻለ 20% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ሠ) ስታርታፑ ከመስራቾቹ ባለፈ ሌሎች አስፈላጊ ሰራተኞችን በመቅጠር ቡድኑ እየሰፋ ስለመሄዱ ወይም አማራጭ የቴክኖሎጂ አቅም መጠቀም እና አደረጃጀት መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ከቻለ 20% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ረ) ስታርታፑ በዚህ የዕድገት ደረጃ ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ዕድሳት ሲመጣ በዚህ አንቀጽ ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሠ) የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቀ ሆኖ በእያንዳንዱ መስፈርት ጉልህ የሆነ መሻሻል ማሳየቱን የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

ሰ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ረ) ላይ የተቀመጠው ራሱን ችሎ ከ100% የሚገመገም ሆኖ እድሳቱን ለማግኘት ከ75% በላይ ማሳካት ይጠበቅበታል፡፡

**3) ተመንዳጊነት እና ሽግግር ደረጃ (Scale and Exit Stage) ስታርታፕ**

በዚህ ደረጃ የሚገኝ ስታርታፕ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፦

ሀ) የስታርታፑ የቢዝነስ እንቅስቃሴ በሀገር ውስጥ ወይም ወደ ጎረቤት ሀገራት ወይም ወደ ዓለምአቀፍ ካምፓኒ በፍጥነት ማደጉን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ 25% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ለ) የስታርታፑ የገበያ ድርሻ በከፍተኛ ሁኔታ (disruptive) የመጨመር ሁኔታን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ 15% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ሐ) ስታርታፑ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) መሰረት የቢዝነስ እንቅስቃሴውን ለመምራት የሚያስችል አስፈላጊ ሰራተኞችን መጨመሩን ወይም አማራጭ የቴክኖሎጂ አቅም መጠቀም እና መዋቅራዊ ሽግግርን የሚያረጋግጥ አደረጃጀት መኖሩ የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ 10% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

መ) ስታርታፑ ከኢንቨስተሮች እና ከሌሎች ፈንድ አድራጊዎች ለመመንደግ የሚውል ፋይናንስ ስለማግኘቱ የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ 20% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ሠ) ከኢንቨስተር፣ ምህዳር ገንቢ እና ሌሎች ስትራቴጂካዊ የቢዝነስ አጋርነት ድጋፍ እንዲሁም የስታርታፕ አሁናዊና የወደፊት ገበያና ኢንቨስትመንት አመላካች እና የእድገት ስትራቴጂ አዎንታዊነት የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ 15% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ረ) ስታርታፑ በገበያው የተረጋጋ ተገማችና አስተማማኝ ቢዝነስ ሆኖ፤ አክሲዮን የመሸጥ ሂደት ወይም ከሌላ ኩባኒያ ጋር የመቀላቀል ወይም ለመሸጥ ዝግጁ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ 15% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

22.<u>የስታርታፕ ስያሜ ዕድሳት</u>

1) በአዋጁ አንቀጽ 13 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ስታርታፑ ስያሜውን ለማሳደስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ መስፈርቶችን ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡

   ሀ) ስታርታፑ ስያሜ ከወሰደበት ቀን ጀምሮ ዕድገቱን በተመለከተ የአፈጻጸም ሪፖርት ማቅረብ

   ለ) ስታርታፑ ካለበት ደረጃ ወደ ቀጣይ ደረጃ ለመሸጋገር የሚያስችሉትን መስፈርቶችን ማሟላቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ የማቅረብ፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልቶ ሲገኝ ሚኒስቴሩ የእድሳት ማመልከቻውን ለስያሜ ኮሚቴ ይልካል፡፡

23.<u>የስታርታፕ ስያሜ እገዳ</u>

በአዋጁ አንቀጽ 14 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ስታርታፑ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ጉዳዮችን ፈጽሞ ከተገኘ ስያሜው ሊያግድ ይችላል፡፡

1) በስያሜ አማካኝነት ያገኛቸውን ማትጊያዎች ከተፈቀደው አላማ ውጪ ተጠቅሞ ሲገኝ፤
2) ከስታርታፑ ካፒታል ውስጥ የመስራቹ ድርሻ ከሃያ አምስት በመቶ በታች ሆኖ ከተገኘ፤
3) የስታርታፕ ምርት ወይም አገልግሎት ስኬታማነትን ሊጎዳ የሚችል የመስራች ወይም የአባላት መጉደል በስያሜ ኮሚቴ ሲረጋገጥ፤

4) በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ስታርታፑ በዕድገቱ ሂደት ውስጥ ከስታርታፕነቱ መገለጫ ወጥቶ መደበኛ የአነስተኛ እና ጥቃቅን ቢዝነስ ሆኖ ከተገኘ፤
5) በዕድሳት ሂደት ወቅት የተሳሳተ ወይም አሳሳች መረጃ ካቀረበ፤

**24.<u>የስታርታፕ ስያሜ መሻር</u>**

1) ማንኛውም ስያሜ ያገኘ ስታርታፕ በአዋጁ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (1) ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሰ) የተደነገገውን ፈጽሞ ከተገኘ ስያሜው ይሻራል፡፡
2) ሆኖም በአዋጁ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ሽ)፣ ንዑስ አንቀጽ (2)፣(3) እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 23 መሰረት ለስያሜው መታገድ ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ማሻሻያ እንዲያደርግ ወይም እንዲያስተካክል እድል ሊሰጠው ይገባል፡፡
3) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 23 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በስያሜ ኮሚቴው በሚሰጥ እድል መሰረት ማሻሻያ ካላደረገ ስያሜው ይሻራል፡፡

**25.<u>የውጭ ሃገር ስታርታፕ</u>**

1) የውጭ ሃገር ስታርታፕ ስያሜ ማግኘት፣ እድሳት፣ እገዳ እና መሻርን በተመለከተ አዋጁ እና በዚህ መመሪያ የተደነገጉት በሙሉ ተፈጻሚነት አላቸው፡፡
2) የውጭ ሀገር ስታርታፕ በአዋጁ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ (3) ከተደነገገው በስተቀር ለስታርታፕ የተሰጠውን መብት በሙሉ የማግኘት መብት አለው፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ስለ ውጭ ሃገር ስታርታፕ ዝቅተኛ ካፒታል መጠን፣ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ በሚመለከት በኢንቨስትመት ቦርድ በሚወጣ መመሪያ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>የስታርታፕ ምህዳር ገንቢ የስያሜ፣ የብቃት መስፈርትና እድሳት</u>

**26.<u>የስታርታፕ ምህዳር ገንቢ</u>**

1) የስታርታፕ ምህዳር ገንቢ ስያሜ የሚከተሉትን መደብ መሰረት ያደረገ ነው፡፡
   ሀ) ኢንኩቤተር
   ለ) አክስለሬተር

ሐ) የጋራ መስሪያ ቦታ

መ) ቬንቸር ካፒታል

ሠ) ኤንጅል ኢንቨስተር

2) የፋይናንስና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት፣ የምርምርና ማበልጸግ ኤጀንሲዎች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ጨምሮ ለስታርታፕ ምስረታ፣ ልማትና ዘላቂነት አስተዋጽኦ የሚያደርግ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ ከተገለጹት ምህዳር ገንቢዎች መካከል ለሚያሟሉት ስያሜ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ አዳዲስ መደብ ሲመጣ በዝርዝሩ ውስጥ ሊካተት ይችላል፡፡

4) የአንድ ፕሮግራም ጊዜ ለመደቡ የተቀመጠውን ዝቅተኛ የቆይታ ጊዜ የሚያሟላ ሆኖ ፕሮግራሙ ተከታታይነት ያለውና በተለያየ ዙር የሚፈጸም መሆን አለበት፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ለተዘረዘሩት መደቦች የተቀመጠው የብቁነት መስፈርት እንደተጠበቀ ሆኖ ዝርዝር የምዘና መስፈርት ማኑዋል ይዘጋጃል፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተዘረዘሩት የስታርታፕ ምህዳር ገንቢ መደብ ስያሜ ለማግኘት በቅድሚያ የንግድ ምዝገባ ወይም የንግድ ፈቃድ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ በህግ ስልጣን ከተሰጠው አካል ማቅረብ አለባቸው፡፡

27.<u>የስታርታፕ ምህዳር ገንቢ ብቁነት መስፈርት</u>

በአዋጁ አንቀጽ 16 የተቀመጠው መስፈርት እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1) **ኢንኩቤተር: -**

ሀ) የመጀመሪያ ደረጃ ስታርታፕን የሚደግፍ ሆኖ የቢዝነስ ልማት፣ የቴክኒክና ምርት፣ የህግና ቁጥጥር፣ የፋይናንስና ኢንቨስትመንት ዝግጁነት፣ የትስስር መፍጠሪያ መድረኮችን እና ሌሎች የስታርታፕ አቅም ግንባታ ፕሮግራም ያለው ወይም በሌላ የስታርታፕ ዕድገት ደረጃ ላይ የሚሰራ አቅም እንዳለው የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ 30% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ለ) በተቋማዊ አደረጃጀት የተደራጁ እና በስታርታፕ ኢንዱስትሪ ውስጥ ያሉ ልምድ ያላቸው ቢያንስ 3 ባለሙያዎች ኖሮት ፕሮግራሙን መምራት የሚያስችል የሰው ሃይል መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ 15% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ሐ) ቢያንስ ከ 6 ወር ያላነሰ የቆይታ ጊዜ፣ የግምገማ እና የክትትል ስርዓት እና ቀጣይነት ያለው የኢንኩቤሽን ፕሮግራም ሰነድ ማስረጃ ማቅረብ 15% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

መ) የስታርታፕን ዕድገት ለማሻሻል ወይም ለመደገፍ የሚያስችል የመስሪያ ቦታ፣ የስራ መሳሪያዎች፣ ከመሰረታዊ ምርት ወይም አገልግሎት ጋር የሚጣጣም መሰረተ ልማት ወይም ፕላትፎርም ያሟላ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ 20% ነጥብ ይሰጠዋል፡

ሠ) አገልግሎት ከሚሰጠው ስታርታፕ ጋር ግልጽ የሆነ የትርፍ ድርሻ መጠንን ጨምሮ ዝርዝር የኢንቨስትመንት መግባቢያ ስምምነት ውል መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅብ 10% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ረ) ከሀገር ውስጥ እና ከውጪ ሀገራት የፈንድ አቅራቢዎች ጋር ስላለው ትስስር መረጃ ማቅረብ 10% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

2) **አክስለሬተር: -**

ሀ) ድህረ መጀመሪያ ደረጃ እና ከዚያ በላይ ያሉ ስታርታፖችን የሚደግፍ ሆኖ የዕድገትና ተመንዳጊነት ስልቶች፣ ለኢንቨስትመንት ዝግጁነት፣ ጥልቀት ያለው የቢዝነስ ሞዴል ወደ ገበያ የመግባት ስልት ፣የአመራርና የተቋማዊ መዋቅር ማሳደግ፣ የህግና ቁጥጥር ማሟላት እና የትስስር መፍጠሪያ መድረኮችን እና ሌሎች የስታርታፕ አቅም ግንባታ ፕሮግራም ያለው ወይም በሌላ የስታርታፕ ዕድገት ደረጃ ላይ አቅም ግንባታ ፕሮግራም የሚሰራ አቅም እንዳለው የሚያሳይ ማስረጃ የሚያቀርብ 25% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ለ) በተቋማዊ አደረጃጀት የተደራጁ እና በስታርታፕ ኢንዱስትሪ ውስጥ ያሉ ልምድ ያላቸው ቢያንስ 3 ባለሙያዎች ኖሮት ፕሮግራሙን መምራት የሚያስችል የሰው ሃይል መኖሩን የሚያሳይ ማስጃ ማቅረብ 15% ይሰጠዋል፡፡

ሐ) ቢያንስ ከ 3 ወር ያላነሰ የቆይታ ጊዜ፣ የግምገማ እና የክትትል ስርዓት እና ቀጣይነት ያለው የአክስለሬተር ፕሮግራም ሰነድ ማስረጃ ማቅረብ 15% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

መ) የስታርታፕን ዕድገት ለማሻሻል ወይም ለመደገፍ የሚያስችል የመስሪያ ቦታ፣ አስፈላጊ የስራ መሳሪያዎች ወይም ዲጂታል የትስስር ፕላትፎርም ያሟላ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ 20% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ሠ) አገልግሎት ከሚሰጠው ስታርታፕ ጋር ግልጽ የሆነ የትርፍ ድርሻ መጠንን ጨምሮ ዝርዝር የኢንቨስትመንት መግባቢያ ስምምነት ውል መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ 15% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ረ) ከሀገር ውስጥ እና ከውጪ ሀገራት የፈንድ አቅራቢዎች ጋር ስላለው ትስስር መረጃ ማቅረብ 10% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

3) የጋራ ሥራ ቦታ: -

ሀ) በተቋማዊ አደረጃጀት የተደራጁ እና በስታርታፕ ኢንዱስትሪ ውስጥ ያሉ ልምድ ያላቸው ቢያንስ 3 ባለሙያዎች ኖሮት ፕሮግራሙን መምራት የሚያስችል የሰው ሃይል መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ 30% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ለ) የመጀመሪያ ደረጃ እና ከዚያ በላይ ያሉ ስታርታፖችን የሚደግፍ ሆኖ የስታርታፕ አባልነት፣ የስታርታፕ ማህበረሰብ ግንባታና ተሳትፎ፣ የሙያና የኢኖቬሽን አገልግሎት እና ሌሎች ተመሳሳይ አቅም ግንባታ ፕሮግራም የሚሰራ አቅም እንዳለው የሚያሳይ ማስረጃ የሚያቀርብ 20% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ሐ) የስታርታፕን ዕድገት ለማሻሻል ወይም ለመደገፍ የሚያስችል የመስሪያ ቦታ፣ አስፈላጊ የስራ መሳሪያዎች ወይም ዲጂታል የትስስር ፕላትፎርም ያሟላ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ 50% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

4) **ቬንቸር ካፒታል:-**

ሀ) ድህረ መጀመሪያ ደረጃ እና ከዚያ በላይ ያሉ ስታርታፖችን የሚደግፍ ሆኖ ፤ ተከታታይነት ያለው ኢንቨስትመንት አቅርቦት፤ የስጋት አስተዳደርና ውጤት አመላካች ክትትል፤ ሃሳቡን የሚያቀርብበት ኢንቨስትመንት መድረክ፤ የገበያ ማስፋፊያና ተመንዳጊነት ድጋፍ፤ የአመራር፤ታለንት፤ መዋቅራዊ አደረጃጀት እና ኦፕሬሽን ዝግጁነት፤ የሽግግር ዕቅድና መዋቅር ዝግጅት ድጋፍ፤ አለማቀፋዊ የትስስር ድጋፍ፤ ወይም በሌላ የስታርታፕ ዕድገት ደረጃ ላይ አቅም ግንባታ ፕሮግራም የሚሰራ አቅም እንዳለው የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ 25% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ለ) በተቋማዊ አደረጃጀት የተደራጁ እና በስታርታፕ ኢንዱስትሪ ውስጥ ያሉ ልምድ ያላቸው ቢያንስ 3 ባለሙያዎች ኖሮት ፕሮግራሙን መምራት የሚያስችል የሰው ሃይል መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ 20% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ሐ) ቢያንስ ከ 5 አመት ያላነሰ የቆይታ ጊዜ፣ የግምገማ እና የክትትል ስርዓት እና ቀጣይነት ያለው የቬንቸር ካፒታል ኢንቨትመንት ፕሮግራም ሰነድ ማስረጃ ማቅረብ 20% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

መ) የስታርታፐን ዕድገት ለማሻሻል ወይም ለመደገፍ የሚያስችል በተለያዩ የስታርታፕ ደረጃዎች የተዋቀረ ኢንቨስትመንት አቅርቦት፤ የመስሪያ ቦታ፣ አስፈላጊ የስራ መሳሪያዎች ወይም ዲጂታል የትስስር ፕላትፎርም ያሟላ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ 15% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ሠ) አገልግሎት ከሚሰጠው ስታርታፕ ጋር ግልጽ የሆነ የትርፍ ድርሻ መጠንን ጨምሮ ዝርዝር የኢንቨስትመንት መግባቢያ ስምምነት ውል መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ 10% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ረ) ከሀገር ውስጥ እና ከውጪ ሀገራት የፈንድ አቅራቢዎች ጋር ስላለው ትስስር መረጃ ማቅረብ 10% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

**5) ኤንጀል ኢንቨስተር:-**

ሀ) የመጀመሪያ፣ ድህረ መጀመሪያ ደረጃ እና ከዚያ በላይ ያሉ ስታርታፖችን የሚደግፍ ሆኖ ተከታታይነት ያለው ኢንቨስትመንት ዝግጁነት እና አቅርቦት፣ ዝግጁነት መረጃ ማጣራትና አቅርቦት መከታተል፣ የኢንቨስትመንት ስጋት ትንተናና መጋራት ስልቶችን መጠቀሙን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ 20% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ለ) የገበያ ማስፋፊያና ትስስር የተግባር ስልጠና እና ማማከር ስራ መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ 15% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ሐ) ስታርታፑን ለቬንቸር ካፒታል ኢንቨስትመንት ብቁ እንዲሆኑ የሚያበቃ፣ የሽግግር ድጋፎችን ያካተተ ፕሮግራም አቅም እንዳለው የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ 15% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

መ) በተቋማዊ አደረጃጀት የተደራጁ እና በስታርታፕ ኢንዱስትሪ ውስጥ ያሉ ልምድ ያላቸው ኤንጀል ኢንቨስተሩን ጨምሮ ቢያንስ 2 ፕሮግራሙን መምራት የሚያስችል የሰው ሃይል መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ 15% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ሠ) የግምገማ፣ የግንኙነት እና የክትትል ስርዓት ድጋፍ አመላካች እና ቀጣይነት ያለው የኤንጀል ኢንቨስትመንት ካፒታል ፕሮግራም ሰነድ ማስረጃ ማቅረብ 15% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ረ) ኤንጅል ኢንቨስተሩ ከተመንዳኒነት እና ሽግግር ደረጃ በኋላ ከሚገኘው ስኬት ላይ ድርሻ ለማግኘት መወሰኑን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረበ 5% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ሰ) የስታርታፐን ዕድገት ለማሻሻል ወይም ለመደገፍ የሚያስችል በተለያዩ ስታርታፕ ደረጃዎች የተዋቀረ ኢንቨስትመንት አቅርቦት፤ የመስሪያ ቦታ፣ አስፈላጊ የስራ መሳሪያዎች ወይም ዲጂታል የትስስር ፕላትፎርም ያሟላ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ 5% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ሸ) አገልግሎት ከሚሰጠው ስታርታፕ ጋር ግልጽ የሆነ የትርፍ ድርሻ መጠንን ጨምሮ ዝርዝር የኢንቨስትመንት መግባቢያ ስምምነት ውል መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ 5% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

ቀ) ከሀገር ውስጥ እና ከውጪ ሀገራት የፈንድ አቅራቢዎች ጋር ስላለው ትስስር መረጃ ማቅረብ 5% ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

## 28.<u>የስታርታፕ ምህዳር ገንቢ ዕድሳት</u>

1) በአዋጁ አንቀጽ 19 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የስታርታፕ ምህዳር ገንቢ ስያሜ ለማሳደስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ መስፈርቶችን ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡

ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 27 ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት፡፡

ለ) ስያሜ ከወሰደበት ቀን ጀምሮ በአመት አንድ ጊዜ የአፈጻጸም ሪፖርት በዲጂታል ፕላትፎርም የማቅረብ፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልቶ ሲገኝ ሚኒስቴሩ ለስያሜ ኮሚቴ ይልካል፡፡

## 29.<u>የስታርታፕ ምህዳር ገንቢ ስያሜ እገዳ</u>

በአዋጁ አንቀጽ 20 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የስታርታፕ ምህዳር ገንቢው ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ጉዳዮችን ፈጽሞ ከተገኘ ስያሜው ሊታገድ ይችላል፡፡

1) በስያሜ አማካኝነት ያገኛቸውን ማትጊያዎች ከተፈቀደው አላማ ውጪ ተጠቅሞ ሲገኝ፤
2) የስታርታፕ ምህዳር ገንቢነት የተቀመጡትን መስፈርቶች አሟልቶ ካልተገኘ፡፡
3) የአፈጻጽም ሪፖርት ማቅረብ ካልቻለ፤

**30.<u>የስታርታፕ ምህዳር ገንቢ ስያሜ መሻር</u>**

በአዋጁ አንቀጽ 21 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የስታርታፕ ምህዳር ገንቢው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 29 የተዘረዘሩትን አሻሽሎ ካልተገኘ ስያሜው ሊሻር ይችላል፡፡

**31.<u>የውጭ ሃገር ስታርታፕ ምህዳር ገንቢ</u>**

1) የውጭ ሃገር ስታርታፕ ምህዳር ገንቢ ስያሜ ማግኘት፣ እድሳት፣ እገዳ እና መሻርን በተመለከተ የአዋጁ ድንጋጌ እና በዚህ መመሪያ ለሀገር ውስጥ ስታርታፕ ምህዳር ገንቢ የተቀመጠ መስፈርት ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡
2) የውጭ ሀገር ስታርታፕ ምህዳር ገንቢ ስያሜ ለማግኘት ማመልከቻ ሲያቀርብ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (4) መሰረት አሟልተው እንዲገኙ ለኢንቨስትመንት ኮሚሽን ይልካል፡፡
3) የውጭ ሀገር ስታርታፕ ምህዳር ገንቢ በአዋጁ አንቀጽ 32 እና 34 ላይ የተደነገገውን ማበረታቻ ያገኛል፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ስለ ውጭ ሃገር ስታርታፕ ምህዳር ገንቢ ዝቅተኛ ካፒታል መጠን፣ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ በሚመለከት በኢንቨስትመት ቦርድ በሚወጣ መመሪያ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሰባት</u>

## <u>የቅሬታ አፈታት</u>

**32.<u>የቅሬታ ኮሚቴው አባላት</u>**

1) በአዋጁ አንቀጽ 22 መሰረት የቅሬታ ኮሚቴው ተጠሪነት ለሚኒስትሩ ሆኖ በውስጡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ አባላትን የያዘ ነው፡፡
   ሀ) ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር .........ሰብሳቢ
   ለ) ገንዘብ ሚኒስቴር................................ አባል
   ሐ) የስራና ክህሎት ሚኒስቴር..............አባል
   መ) ትምህርት ሚኒስቴር.......................... አባል
   ሠ) ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር...... አባል

ረ) ኢንደስትሪ ሚኒስቴር.........................አባል

ሰ) ኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት...... አባል

ሸ) በዘርፉ ካሉ የሙያ ማህበራት ተወካይ..........................አባል ናቸው፡፡

2) የኮሚቴው አባል ተቋማት በተቋማቱ የበላይ ኃላፊዎች በሚወከል ኃላፊ ወይም ባለሙያ የሚወከሉ ይሆናል፡፡

3) ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑ በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ ይቆጠራል፡፡

4) የኮሚቴው ውሳኔ በስምምነት ወይም በድምጸ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጹ እኩል በኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

5) የስታርታፕ አስተዳደራዊ ጉዳይን የሚመለከት ሰው በቅሬታ ኮሚቴ አባልነት ሊሰየም አይችልም፡፡

33.<u>የቅሬታ ኮሚቴ ተግባርና ሃላፊነት</u>

1) በአዋጁ አንቀጽ 22 መሰረት የተቋቋመው የቅሬታ ኮሚቴ የሚቀርቡ የቅሬታ ማመልከቻዎችን ይቀበላል፡፡

2) የቀረቡት የቅሬታ ማመልከቻ የቴክኒክ ጉዳይ ሆኖ ሲገኝ የቅሬታ ኮሚቴው ማመልከቻውን በ3 የስራ ቀናት ውስጥ ለስያሜ ኮሚቴው ይልካል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የስያሜ ኮሚቴው ቅሬታው በደረሰው በ15 የስራ ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

4) ቅሬታው አስተዳራዊ ሆኖ ሲገኝ የቅሬታ ኮሚቴ ጉዳዩን መርምሮ በ15 የስራ ቀናት ውስጥ የመጀመሪያውን ውሳኔ ማጽናት፣ ሊሽረው ወይም ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

34.<u>የቅሬታ አቀራረብ</u>

1) ከስታርታፕ ስያሜ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ቅሬታ ያለው ማንኛውም አካል ለቅሬታው ምክንያት የሆነው ውሳኔው በደረሰው በ15 የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በፖርታሉ በኩል ለቅሬታ ኮሚቴው ማቅረብ ይችላል፡፡

2) ኮሚቴው በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ቅሬታውን በ30 ቀናት ውስጥ ለሚኒስትሩ የማቅረብ ይችላል፡፡

3) በሚኒስትሩ ውሳኔ ቅሬታ የተሰማው ወገን ሥልጣን ላለው ፍርድቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡

35.<u>የቅሬታ ኮሚቴ የአገልግሎት ጊዜ</u>

1) የቅሬታ ኮሚቴው የአገልግሎት ጊዜ ሁለት አመት ነው፡፡
2) እንደአስፈላጊነቱ ለተጨማሪ አንድ ዙር ሊመረጥ ይችላል፡፡

36.<u>የጥቅም ግጭት አፈታት</u>

1) ማንኛውም የኮሚቴ አባል ስራ ከመጀመሩ በፊት በተሰጠው ሥራ ላይ ገለልተኛነቱን ሊጎዳ ወይም እንደሚጎዳ ሊታይ የሚችል ማንኛውንም የግል፣ የፋይናንስ፣ የሙያ ወይም የንግድ ጥቅም ወይም ግንኙነት ካለ ማሳወቅ እንዳለበት የሚያስገድድ ቅጽ በመሙላት በፊርማው ማረጋገጥ አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ አባሉ የሚያሳውቀው ጥቅም ግንኙነት እንዳለ እንዳወቀ ከሚመለከተው ግምገማ ወይም ውሳኔ በፊት መቅረብ አለበት፡፡
3) የጥቅም ግጭት እንዳለው ያስታወቀ የኮሚቴ አባል ከተመለከተው ግምገማ ወይም ውሳኔ ላይ ተሳትፎ እንዳያደርግ መደረግ አለበት፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተገለጸው ቅጽ የመመሪያው አባሪ ቁጥር 2 ሆኖ ተካቷል፡፡

## <u>ክፍል ስምንት</u>

## <u>ልዩልዩ ድንጋጌዎች</u>

37. <u>መመሪያ ስለማሻሻል</u>

ይህን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በማንኛውም ጊዜ ሚኒስቴሩ መመሪያውን ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

38.<u>የመተባበር ግዴታ</u>

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ደርሻ ያለው ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

39. <u>ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>

ይህንን መመሪያ የሚጣረስ ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

40.<u>የመመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በሚኒስቴሩ ድረገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ፣ ጥቅምት፣ 2019 ዓ.ም**

**ፍሬሕይወት ታምሩ**

**የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር**

**ሚኒስትር**